# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## በአኙዋክ ወገኖቻችን ላይ የታቀደውን ጥቃት አጥብቀን እንቃወማለን

የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባገነን አገዛዝ ወኪሎችና የደቡብ ሱዳን ባለሥልጣኖች ሰሞኑን በጋምቤላ ከተማ ተገናኝተው ባካሄዱት ስብሰባ ደቡብ ሱዳን ውስጥ በስደት ላይ እየተንገላቱ ያሉትን የአኙዋክ ብሔረሰብ አባላት በኃይልና በግድ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ስምምነት ላይ መድረሳቸው ታውቋል፡፡

በሜስተር ሬይክ መቻር የሚመራው የደቡብ ሱዳን መንግሥት የጋምቤላ ብሔረሰብ አባላትን በተለይም የአኙዋክ ብሔረሰብ አባላትን በወታደራዊ ኃይል አስገድዶ ለወያኔ መንግሥት ለማስረከብ መስማማቱ በጣም አሳዛኝና የሚወገዝ ድርጊት ነው፡፡ ይህ ርምጃ የስደተኞችን የሰብዓዊ መብትና የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የሚጥስ ሕገ ወጥ፥ አደገኛና አሳዛኝ ርምጃ በመሆኑ  የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ድርጊቱን በጽኑ ይቃወማል፡፡

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በተላየዩ የሀገራችን ክፍሎች በሕዝባችን ላይ በርካታ በደሎችን ሲፈጽም  የቆየና አሁንም በተጠናከረ መንገድ እያከሄደ መሆኑ ግልጽ ሲሆን በተለይ በአኙዋክ ብሐረሰብ ወገኖቻችን ላይ በየጊዜው የተካሄዱት ጭፍጨፋዎችና ግድያዎች በከፍተኛ ሀዘን የምናስታውሳቸው ናቸው፡፡ በህዳር 12 ቀን 1996 ዓ./ም የአቶ መለሰ አምባገነን አገዛዝ ጋምቤላ ውስጥ ያካሄደው አሰቃቂ ጭፍጨፋ በመቶ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ሕይወት ያጠፋና ብዙዎቹን አካለ ስንኩላን ያደረገ አረመኔያዊ እርምጃ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት በርካታ ሴት እህቶቻችን ክብረ ንጽህናቸው ተደፍሯል፥ የብዙ አኙዋክ ብሔረሰብ ቤትና ንብረት ወድሟል፥ ብዙዎቹም  ለእስር ተዳርገዋል፡፡ ከህዳር 96 በፊትና ከዚያም በኋላ በተለያዩ ጊዜያት የሕወሓት/ኢሕአዴግ ወታደሮች ብዙ አሰቃቂና ዘግናኝ ግፎች በአኙዋኩ ብሔረሰብ ላይ ፈጽመዋል፡፡ ከእነዚህ አሰቃቂ ጭፍጨፋዎች ለመማምለጥና ህይወታቸውን ለማትረፍ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የአኙዋክ ብሐረሰብ ወገኖቻችን ወደ ደቡብ ሱዳን በመሄድ ዛሬ በተለያዩ ካምፖች ውስጥ እየተቸገሩና እየተንገላቱ በስደተኛነት በመኖር ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ወገኖች በኃይል ለመመለስ የሚደረገው ሙከራ ኢሰብአዊ ከመሆኑም በላይ የዓለም አቀፍ ስምምነትን በመጣስ በሕግ የሚያስጠይቅ ርምጃ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በሱዳን ማዕከላዊ መንግሥት ወታደሮች ያለ ፍላጎታቸው እየተያዙ ለጨፍጫፊው የመለሰ መንግሥት ወታደሮች ሲሰጡ ይህ የመጀመሪያው አይደለም፡፡ በተለያዩ ጊዚያት ኢትዮጵያውያን ከካርቱምና ከገዳሪፍ ከተሞች እንዲሁም ከተለያዩ የስደተኞች ካምፖች እየታደኑና እየታፈኑ ለአምባገነኑ መንግሥት ተሰጥተዋል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች የበላይ ኮሚሽንም ከስደተኞቹ በየጊዜው የቀረቡትን ጥያቄዎችና ልመናዎች ተቀብሎ አስፈላጊ የሆኑ ርምጃዎች የወሰደባቸው ሁኔታዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ይህም ድርጊት ስደተኞችንና  ሰላም ወዳጹን ሕዝብ በጽኑ ሲያሳዝን ቆይቷል፡፡


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

የአኙዋክ ብሔረሰብ አባላትን ግፍና ጭፍጨፋን በመሸሸሽ ከሰፈረቡት የስደተኛ ካምፕ አፈናቅሎ ኃይልን በመጠቀም አስገድዶ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ የሚደረገው ዕቅድ በከፍተኛ ደረጃ መወገዝ ያለበት ነው። ይህ አረመኔያዊ እርምጃ ባስቸኳይ እንዲቆም የተባባሩት መንግሥታትና የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽንና ጉዳዮ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጥብቅ ርምጃ እንዲወስዱ ኅብረቱ እየጠየቀ በዚህ ጉዳይ ላይ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እንደተለመደው ድምጻቸውን እንዲያሰሙና የሚችሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ ይማጸናል።

ኢትዮጵያውያን ወገኖች በዚህ ጉዳይ ያላቸውን የተቃውሞ ድምፅ ባለማቋረጥ ለተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ  የስደተኞች ኮሚሽን፥ ለመንግሥታትና ለሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች እንዲያሰሙ እንጠይቃለን።

ኢዴኃኅ
መስከረም 30 ቀን 1999 ዓ.ም.